# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት አንድ (1ኛ ጴጥ 1፡1-5)

1. ስለጸሐፊው የምናውቃቸው ነገሮች፡ ሐዋርያ መሆኑንና ስሙ ደግሞ ጴጥሮስ እንደሆነ ሲሆን ስለተጻፈላቸው ሰዎች ደግሞ የእግዚአብሄር ምርጦች እንደሆኑ፣ ተበትነው በመጻተኛነት እንደሚኖሩ፣ እግዚአብሄር አስቀድሞ ያወቃቸው ናቸው፣ በደሙ የተረጩ ናቸው፣ በመንፈስ ደግሞ የተቀደሱ ናቸው፡፡
2. የአብ አስቀድሞ ማወቅና መምረጥ፣ በወልድ ደም መረጨትና በመንፈስ ቅዱስ መቀደሳችን የሥላሴዎችን ተሳትፎ በግልጽ ያረጋግጥልናል፡፡
3. ከታላቅ ምህረቱ የተነሳ…ለማይጠፋ፣ ለማይበላሽና ለማይለወጥ ርስት እንደገና ስለወለደን ነው ይህንን ምስጋና ማቅረብ የፈለገው፡፡
4. በኢየሱስ ሞት የተገኙት በዚህ ክፍል የምናያቸው አንደኛው አዲስ ልደት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ርስት ናቸው፡፡
5. ስለርስታችን የተነገሩት ሶስት ነገሮች፤ 1) የማይጠፋ 2) የማይለወጥና 3) የማይበላሽ ናቸው፡፡
6. ይህ በመጨረሻ የሚገለጥ ድነት ብሎ የሚጠቅሰው በተሟላ ሁኔታ የነፍስ ብቻ ሳይሆን ሥጋችንንም ጨምሮ የሚሞተው የማይሞተውን፣ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን የሚለብስበትንና ደህንነታችን ፍጹም የሚሆንበትን ጊዜ የሚያመለክት ነው፡፡
7. ‹‹ተጠብቃችኋል›› ከሚለው አነጋገር የደህንነታችን ጠባቂ እግዚአብሄር መሆኑን ያሳያል፡፡ በቁ2 ላይ የእግዚአብሄርን ማወቅና መምረጥ ስለሚናገር፣ በዚህ ክፍል ደግሞ እስከመጨረሻው በእርሱ መጠበቃችንን ስናይ ደህንነታችን በእርሱ ተጀምሮ በእርሱ እንደሚጨረስ እንገነዘባለን፡፡
8. ሰው ትልቁ ችግሩ የተስፋ ማጣት በመሆኑ እነዚህን ሰዎች ከፊታቸው ስላለው ታላቅ ተስፋ ማስተማሩ ልባቸው በአሁኑ ላይ እንዳያርፍና በዘለዓለሙ ላይ እንዲያተኩሩ ይረዳቸዋል፡፡
9. ለእያንዳንዱ ሃሳቡን ለመግለጽ እድል ይስጠው፡፡

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ሁለት (1ኛ ጴጥ 1፡6፡12)

1. መከራቸው ለጥቂት ጊዜ መሆኑን ነው የሚነግራቸው። የመከራቸውን ጊዜ አጭር አድርጎ የሚናገርበት ምክንያት ሰው እድሜውን ሁሉ እንኳን በመከራ ቢኖር ከዘለዓለም ጋራ ሲተያይ ከቁጥር ስለማይገባ ነው። ስለፈተናቸው ሌላ የሚናገረው፤ የጊዜውን እጥረት ብቻ ሳይሆን ብዛቱንም ጨምሮ ይናገራል።
2. እነዚህ ሰዎች በመከራቸው እጅግ ደስ እንደሚላቸው ነው ጴጥሮስ የሚናገረው። የዚህ ዓይነቱ አነጋገር ለሥጋዊ ሰው ሞኝነትና የሚስቅበት ንግግር ነው።
3. የከበረው እምነታቸውን እውነተኛነት ለማረጋገጥና ጌታ ሲገለጥ ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ምስጋናን ያስገኝ ዘንድ ነው። መከራን ስናልፍ ልንዘነጋው የማይገባን አንድ እውነት ቢኖር ለአጭር ጊዜ መሆኑን ማወቅ ነው።
4. የወርቅ ጥራት የሚታወቀው በእሳት እንደሆነ የእምነታችንም ጥራትና እውነተኛነት የሚለካው በመከራ ውስጥ ስናልፍ በመሆኑ ነው። ኢየሱስን ሳያዩት ይወዱታል ደግሞም ያምኑታል።
5. ጌታን ስንቀበል ከሃጥያት ባርነት ነጻ እንደምንወጣና እንደምንድን ሲሆን በዚህ ክፍል የሚነገረው ደህንነት ደግሞ ከሃጥያት ሃይል የምንድነውን ደህንነት ነው።
6. ለእኛ ስለተነገረው ትንቢት በጥንቃቄ ይመረምሩ ነበር።
7. ይህ ነብያቱ በጥንቃቄ የሚመረምሩትና መላዕክቱ ሊያዩት የሚመኙት ደህንነታችን እንደቀላልና ርካሽ ነገር ልንቆጥረው የማይገባን እጅግ የተከበረ ነገር መሆኑን ይጠቁመናል።
8. እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ ይግለጥ።

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ሶስት (1ኛ ጴጥ 1፡13-25)

1. ‹‹ስለዚህ›› በሚለው ቃል ማያያዝ የፈለገው፤ ከዚያ በፊት የዘረዘረውን የደህንነታችንን ክቡርነትና ታላቅነት ካሳየን በኋላ ይህ የከበረ ነገር ደግሞ ከእኛ የሚጠይቅብን ነገር እንዳለ በመጠቆም ሁለቱን ለማገናኘት ነው። እንዲያደርጉ የጠየቃቸውም፡ ልቡናቸውን እንዲያዘጋጁ፣ ራሳቸውን እንዲገዙና ተስፋቸውን ደግሞ ጌታ ሲገለጥ በሚሰጣቸው ጸጋ ላይ እንዲያደርጉ ነው።
2. እነዚህ አማኞች በተስፋ ላይ እንዲያተኩሩ የሚመክርበት ዋነኛ ምክንያት በዓለም ላይ ተስፋ ሊጣልበት የሚችል ነገር እንደሌለና የኢየሱስ ክርስቶስ የመገለጡ ተስፋ ግን የማይቀርና አማኝ ሁልጊዜ ልቡን ሊጥልበት የሚገባ በመሆኑ ነው።
3. አንደኛው ቀድሞ ይከተሉት የነበረውን ክፉ ምኞት እንዳይከተሉና ሁለተኛው ደግሞ ቅዱሱን እግዚአብሄርን በቅድስናው እንዲመስሉት ነው። እግዚአብሄርን የመምሰል ቅድስና ጳውሎስ በፊሊ. 3፡12-14 እንደሚናገረው የአማኝ ዕለት በዕለት ግቡ አድርጎ መኖር ያለበት ነገር እንደሆነ እንማራለን።
4. በእግዚአብሄር ዘንድ አድልዎ እንደሌለ ነው። በዚህ ክፍል የምናነበው ፍርሃት ከአክብሮት የተነሳ የምንፈራውን አይነት ፍርሃት ነው። አባታችን ስለሆነ እንዳያዝንብን ስለምንፈልግ ይህንን እናደርጋለን።
5. የቀድሞ ህይወታቸው በከንቱነት የተሞላ እንደነበረ ነው የሚያስታውሳቸው። ከቀድሞ አባቶቻችሁ የወረሳችሁት ሲል ርካሽና እግዚአብሄርን የማያስከብር ምግባሮች ሊሆን ይችላል።
6. የተገዙበት የክርስቶስ ደም ምን ያህል ክቡርነቱን ለማሳየት ነው።
7. በዚህ ክፍል ወንድሞቻችንን ስለመውደድ የታዘዝንበት መጠን ‹‹አጥብቀን›› ‹‹ከልብ›› የሆነ መዋደድን ይጠይቀናል። ዳግመኛ መወለዳችን ልዩ ፍጥረት እንደሆንና ብቃትን ከዚህ የተነሳ እንዳገኘን የሚጠቁመን ነው።
8. ይህንን እውነት መረዳት ነገሮች ሁሉ ሃላፊ እንደሆኑና ከወንድሞቻችን ጋራ ተጣልተንም ሆነ ገፍተናቸው የምናገኘው ነገር ሁሉ ፍጻሜአቸው አጭር እንደሆነ ስናውቅ በዘለዓለሙ ላይ እንድናተኩር ይረዳናል።
9. በእያንዳንዱ ተሳታፊ ይመለስ።

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት አራት (1ኛ ጴጥ 2፡1-12)

1. አማኞች በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እንዲያደርጉ የሚጠየቁት፤ ክፋትን፣ ማታለልን፣ ግብዝነትን፣ ቅናትንና ሐሜትን እንዲያስወግዱ፤ እንዲሁም ንጹሑን መንፈሳዊ ወተት እንዲመኙ ነው። ለዚህም የሰጣቸው ምክንያት ጌታ መልካም መሆኑን ስለቀመሱ ነው።
2. ድንጋዩ፡ በሰው ዘንድ የተናቀ ነው፣ በእግዚአብሔር ዘንድ የተመረጠ ነው፣ ክቡር ነው፣ ድንጋዩ ሕያው ነው።
3. እናንተ ደግሞ የሚለው አማኞችን ነው። ቅዱስ ካህናት ናቸው፣ መንፈሳዊ ቤት ናቸው።
4. ይህ አነጋገር እርሱ በሚፈልገው መንገድ ለመሰራት ካስፈለገ ወደ እርሱ መቅረብ፣ ከእርሱ ጋራ መጣበቅንና ሁልጊዜ ከእርሱ ጋራ ግንኙነታችን የርቀት መሆን እንደሌለበት ያስገነዝበናል።
5. በዚህ ቁጥር ላይ እናንተ እያለ የሚናገረው አማኞችን ነው። እነዚህ ሰዎች ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን የተጠሩ ናቸው፣ የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ የሚያውጁ ናቸው፣ በእርሱ የተመረጡ ናቸው፣ የንጉሥ ካህናት ናቸው፣ ቅዱስ ሕዝብ ናቸው፣ አሁን የእግዚአብሄር ሕዝብ ናቸው፣ አሁን ምህረት ያገኙ ናቸው።
6. በዚህ ዓለም እንግዶችና መጻተኞች ስለሆኑ ነው። ይህ ሥጋዊ ምኞት የሚያጠቃልለውን ጥቂት ነገሮች በመዘርዘር ተወያዩባቸው።
7. ‹‹እንግዳና መጻተኛ›› ቋሚ ቤት የሌለው፣ መኖሪያው ሌላ ቦታ የሆነ፣ ብዙ ቁሳቁስ የሌለው፣ ልቡንና ሐሳቡን በሚኖርበት ያላሳረፈ….ወዘተ። አማኝ ሌላ መኖርያ ስለተዘጋጀለትና ይህ የአጭር ጊዜ መኖሪያው ስለሆነ በዚህ ዓይነት ሊኖር ይገባል። እንደዚህ ለመኖር የምንቸገርባቸው ብዙ ምክንያቶችን መጥቀስ እንችላለን፤ ነገር ግን ዋነኛው የዓለምን አኗኗር በማየት እንደነሱ መኖር እንዳለብን ስለሚመስለን ነው።
8. እያንዳንዱ ያለውን ሃሳብ ይለዋወጥ።

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት አምስት (1ኛ ጴጥ 2፡13-25)

1. በዚህ ክፍል አማኞች እንዲያደርጉ የሚታዘዙት ነገር፡ ለምድራዊ ባለሥልጣን ሁሉ እንዲታዘዙ ነው። የሰጣቸውም ምክንያት መልካም በማድረግ የአላዋቂዎችን ከንቱ ንግግር ዝም ማሰኘታቸው የእግዚአብሄር ፈቃድ ስለሆነ ነው።
2. እነዚህ ሁለት ሃሳቦች የሚቃረኑ አይደሉም፤ ምክንያቱም አማኝ ከሃጥያትና ከህግ ነጻ ወጥቷል። ነጻነቱ ግን ለጽድቅ ለመገዛት እንጂ ያለበለዚያ ነጻነቱ ነጻነት አይሆንም። ይህንን ሃሳብ በበለጠ ለመረዳት ሮሜ 6፡19 ኝን መመልከት ይረዳል።
3. ለሰው ሁሉ ተገቢውን አክብሮት እንዲሰጡ፣ ወንድሞችን እንዲወዱ፣ እግዚአብሄርን እንዲፈሩና ንጉስን እንዲያከብሩ ነው። ሰው ሁሉ በእግዚአብሄር ምስል የተፈጠረ ከመሆኑ የተነሳ ልንሰጠው የሚገባን ክብር አለ ማለቱ ነው። ይህም ሰው ስለሆነ ብቻ ነው።
4. አዎን ልዩነት አለ። በቁ16 ላይ አገልጋይ ተብለው የተጠቀሱት አማኞች ሁሉ ሲሆኑ አገልጋይነታቸውም ለእግዚአብሔር ነው፤ በቁ18 ላይ ግን በባርነት ተሸጠው የሚገኙትን አማኞች ብቻ የሚያጠቃልል ነው። እነዚህን የሚያዛቸው ለደጎች ብቻ ሳይሆን ለክፉዎችም በፍጹም አክብሮት እንዲታዘዙ ነው። እኛም በሥራችን ላይ ይህንኑ ትዕዛዝ በመከተል ልንታዘዝ ይገባናል።
5. እነዚህ ሁለት አባባሎች የሚጠቁሙን፤ አንደኛው ትዕዛዙ ለአማኞች ብቻ እንደሆነና የሚታዘዙት ደግሞ ቀላል ወይም የሚወዱት ስለሆነ ወይም ደግሞ ለሌላ ምክንያት ሳይሆን ጌታን ስለሚወዱና ስለጌታ ሲሉ ነው።
6. ማንኛውም ባሪያ ለጌታው በግዱ ይገዛል ሆኖም የአማኝን መገዛት የሚለየው ለጌታ ለኢየሱስ እንደሚገዛና እርሱን እንደሚያገለግል ሆኖ ስለሚያደርግ ነው።
7. በዚህ ክፍል ልንከተለው የተነገረን ምሳሌነቱ ስለ እግዚአብሄር ስንል መከራን መታገስን እንደሚኖርብን ነው። መከራን በትዕግስት ማሳለፍና መቻል ከአማኝ ህይወት የሚጠበቅ ነገር መሆኑን እንማራለን።
8. የተማራችሁትንና ያለፋችሁበትን ልምምድ በማንሳት ተወያዩባቸው።

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ስድስት (1ኛ ጴጥ 3፡1-7)

1. አገልጋዮችን በቁ18 ላይ ለበጎም ለክፉም ጌቶቻቸው ለጌታ ብለው እንዲገዙ የተናገራቸው ለእነርሱም እንደሚሰራና በመንገር ሃሳቡን ለማያያዝ ነው።
2. ሚስቶችን በዚህ ክፍል የሚመክራቸው፤ ለባሎቻቸው እንዲገዙ ሲሆን ንጹህና አክብሮት የተሞላው ህይወትን ቢኖሩ ፍሬው የማያምኑ ባሎቻቸው በህይወታቸው ተማርከው ወደ ክርስቶስ ይመለሳሉ ይላቸዋል።
3. ዋና ጥቅል ሃሳቡ ውበታቸው በውጫዊ ነገር ሳይሆን ውስጣዊ ውበት ላይ እንዲያተኩሩ ሲሆን ይህንን የተለያዩ ነገሮችን የዘረዘረ ሲሆን አንስታችሁ ተወያዩባቸው።
4. እንዲማሩ የተጠየቁት ተስፋቸውን በእግዚአብሄር ላይ ከጣሉ ከቀድሞ ቅዱሳት ሴቶችና በተለይም ደግሞ ከአብርሃም ሚስት ከሳራ እንዲማሩ ተጠይቀዋል።
5. በተለይም ሳራን በምሳሌነት ያስቀመጣት ለባሏ ለአብርሃም በትህትና የመታዘዝ ባህርይ ስላሳየች ነው።
6. ሰዎች ውበት ብለው ላይቆጥሩት ወይም ላይታያቸው ቢችልም እንኳን እግዚአብሄር የሚረካበትና የምደሰትበት እንዲሁም ውበት ብሎ የሚጠራው የውጭውን ሳይሆን የውስጡን በመሆኑ ይህንን ተስፋ በማድረግ በዚህ እውነት መራመዳቸው ነው።
7. ባሎች ደግሞ ለሚስቶቻቸው የሚያስቡ እንዲሆኑና በተጨማሪም ደግሞ እንዲያከብሯቸው ታዞዋል።
8. ደካማ የሚለው አነጋገር ምናልባትም ሴቶች ስሜታቸው በቀላሉ የሚጎዳ መሆኑንና ከዚህም የተነሳ ጥንቃቄ ሊደረግላቸው እንደሚገባ መናገሩ ይሆናል።
9. ባሎች ሚስቶቻቸውን እንዲያከብሩ የተነገራቸው ሁለት ምክንያቶች፤ ሴቶች ደካሞች መሆናቸውና የህይወትን በረከት ደግሞ አብረው የሚወርሱ መሆናቸው ናቸው።
10. እያንዳንዱ ሃሳቡን ይስጥበት።

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ሰባት (1ኛ ጴጥ 3፡8-22)

1. በዚህ ቁጥር ላይ ‹‹ሁላችሁ›› ሲል የሚያጠቃልለው አማኞችን በሙሉ ማለትም ባሪያ ጌታ፣ ሚስት ባል፣ ልጅ አባትና ሌሎችንም ሁሉ ነው፡፡
2. ሁሉም በአንድ ሃሳብ እንዲስማሙ፣እርስ በእርስ እንዲተሳሰቡ፣እንደወንድማማች እንዲዋደዱ፣ርህሩሆችና ትሁታን እንዲሆኑ ሲሆን እንዳይለማመዱት የሚመክራቸው ደግሞ ክፉን በክፉ ወይም ስድብን በስድብ መመለስን ነው፡፡ ክፉ የሚለው የማንወደው ወይም የማይገቡ ነገሮችን ሰዎች ሲያደርጉብን ማለት ነው፡፡
3. ይህ ክፍል ጥሪያችንን የሚያያይዘው መልካምን ከማድረግ ጋራና እንዲሁም በረከትን ከመውረሳችንም ጋራ ነው፡፡ በጥሪያችንና ኑሯችን ሊነጣጠሉ የማይችሉ ዘወትር እጅ ለእጅ ተያይዘው መሄድ ያለባቸው ነገሮች መሆናቸውን ይህ ክፍል ያስተምረናል፡፡
4. ይህ በረከት የሚለው ሃሳብ ማናቸውም ሰማያዊም ሆነ ምድራዊ እግዚአብሄር ለእኛ ያዘጋጀልንን በረከት ሊሆን ይችላል፡፡
5. ምላሱን ከክፉ መከልከል፣ ከንፈሮቹ ክፉ ክፉ ከመናገር መከልከል፣ ከክፉ መራቅ፣ መልካምን ማድረግ፣ ሰላምን መፈለግና መከተል ናቸው፡፡ እነኚህ የሚሰሩት ሮሜ 12፡18ትን ስናነብ ራሳችንን በተመለከተ እንጂ አንዳንዴ አስቸጋሪ የሚሆንበት ጊዜ አለ፡፡
6. ይህንን ማለቱ አይደለም፡፡ በልባችሁ ቀድሱት ሲል የይምሰል ስሙን መጥራት፣ የየሱስ ነኝ ማለት ብቻ ሳይሆን የተለየ፣የከበረ፣ትልቅ ቦታ እንዳለው ንጉስ አድርጋችሁ ቦታ በልባችሁ ስጡት ማለቱ ነው፡፡
7. ይህ ክፍል አማኝ አሉት ከሚላቸው ሁለት ነገሮች የመጀመሪያው ተስፋ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ መልካም ጸባይ ናቸው፡፡ አማኞች ስለተስፋችን ይጠይቃሉ፤ መልካም ጸባያችንን በተመለከተ ደግሞ አክፋፍተው ሊናገሩ እንደሚችሉ ይነግረናል፡፡
8. መከራን መቀበላችን የእግዚአብሄር ፈቃድ የሚሆንበት ጊዜ እንዳለ ይጠቁመናል፡፡ ጌታ የሱስ በ1ኛ ጴጥ 2፡21 እንዳየነው እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ የመጣን መከራ እንዴት እንደምናስተናግደው ምሳሌን ትቶልናል፡፡
9. ክፉን በክፉ እንዳይመልሱ ነገር ግን እነዲባርኩ የሚሉት ተጠቅሰዋል፡፡
10. እያንዳንዱ ተካፋይ ሃሳብ የሚሰጥበት ጊዜ ይሰጠው፡፡

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ስምንት (1ኛ ጴጥ 4፡1-11)

1. መከራን በሥጋው መከራን ሲቀበል የነበረውን አመለካከት እኛም ይህንኑ ዓይነት አመለካከት ከማዳበት አንጻር ነው የተነገረን፡፡
2. አማኝ ከላይ የተጠቀሰው ዓይነት አመለካከት ይዞ ሲኖር በምድራዊ ህይወቱ እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ምኞት እንዳይኖር ይረዳዋል፡፡ ይህም ማለት በመዳራት፣በስካር፣በጭፈራ፣ያለልክ በመጠጣት፣ በባዕድ አምልኮና የመሳሰሉትና ባለማድረግ የለውጡ እውነተኛነት ይገለጣል፡፡
3. በዚሁ ዓላማ (same attitude) የሚለው ሃሳብ ልናደርግ ስለምናስበው ነገር በቅድሚያ አመለካከታችን የተለወጠ እንዲሆን ማስፈለጉን ከክፍሉ ስናይ በተጨማሪም ደግሞ ሮሜ 12፡1-2ትን ስናነብ ለውጥ የሚጀምረው ከአስተሳሰብ ወይም አመለካከት መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡
4. ይህንን ማለቱ አይደለም፡፡ መከራን የተቀበለ የሚለው ከክርስቶስ መከራ ጋራ አያይዞ ስለሆነ እርሱ መከራ ተቀብሎ በሥጋው እንደሞተ እኛም ከሃጥያት መላቀቅና ነጻ መውጣት የምንችለው ሥጋችንን ሲሞት መሆኑን ሲያስገነዝበን ነው፡፡ ሮሜ 6፡7ትንና ገላ 2፡20ን መመልከት ይረዳል፡፡
5. እዚህ ላይ ‹‹የሁሉ ነገር መጨረሻ›› በመባል የተነገረው ስለ ጌታ መምጣት ነው፡፡ 1ኛ ቆሮ 15፡24 ተመልከት፡፡
6. አዕምሯችን በብዙ ነገሮች አለመያዙን፣ የጸዳና ርኩሰት የሌለበት መሆኑ ሁሉ ለጸሎት እጅግ አስፈላጊ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በፈለግነውና በመረጥነው ጊዜ ብቻ የምናደርገው ነገር እንዳይሆን ራስን መግዛት የሚለው ደግሞ ሊኖረን ግድ ነው፡፡
7. ይህ አባባሉ ሰዎች ሲያጠፉ አትናገሩ ዝም በሏቸው ሳይሆን፤ ሰዎች ብዙ ቢበድሉንና ቢያሳዝኑንም እውነተኛ ፍቅር ካለን የማለፍና ይቅር የማለት ችሎታ ይኖረናል ለማለት የተነገረ ሲሆን እርስ በእርሳችን ለመቻቻል ካስፈለገ ይህንን ልንለማመድ ግድ ነው፡፡
8. ጸሎት፣ ፍቅር፣ እርስ በእርስእንግድነት መቀባበልና፣ በተሰጠን የጸጋ ስጦታ ሌሎችን ማገልገል፡፡
9. ነገ አደርገዋለሁ ወይም ቆይ ይደርሳል ብለን የተውነው ነገር ከሆነ የነገር ሁሉ መጨረሻ መቃረቡንና የጌታ መምጣቱ በደጅ መሆኑ ሲነገረን የነገሩን አስቸኳይነትና ጊዜ የሚሰጠው ነገር እንዳልሆነ እናያለን፡፡ ሌላውን ጥያቄ እያንዳንዱ ሰው ይመልሰው፡፡

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ዘጠኝ (1ኛ ጴጥ 4፡12-19)

1. መከራ ለአማኝ እንደ እንግዳ ነገር ሆኖ ሊቆጠር እንደማይገባና እንዲያውም በመከራው ደስተኛ መሆን እንደሚኖርበት እንማራለን።
2. አንዳንዶች ክርስትያን መከራ ሊያገኘው አይገባም፣ ሌሎች ደግሞ መከራ የሚገጥመው በእምነቱ ደካማ ከሆነ ነው፣ መከራ ከገጠመን ክፉ ስለተናገርን ወይም ስላሰብን ነው የሚሉና የመሳሰሉት ይመስላሉ። አማኝ መከራን ለእድገቱ የሚጠቀምበትና በደስታ የሚያስተናግደው የተነገረን ሲሆን ያላመነ ሰው ግን መከራ ከእግዚአብሄር ሃሳብ ጋራ ሊያያዝለት ስለማይችል በደስታ ሊቀበለው አይችልም።
3. በቁ13 መሰረት አማኝ ይህንን ደስታ የሚለማመደው አሁን በመከራው ሲያልፍና ደግሞ ጌታው ሲገለጥም ደስታውን ይለማመዳል።
4. ዛሬ እኛ በምንኖርበት ምድር ለጌታ መከራ መቀበል የምንችልባቸው የተለያዩ ሁኔታዎች አሉ እነዚህንም እያንዳንዱ ተካፋይ ሃሳብ ይስጥና ተወያዩባቸው።
5. ከዚህ ውስጥ ልናያቸው የምንችላቸው ሁለት ሃሳቦች፤ መከራው በእሳት መመሰሉ ከባድነቱን ሲጠቁመን፣ ‹‹የሚፈትን›› የሚለው ደግሞ ወርቅ በእሳት ተፈትኖ ወርቅነቱ እንደሚታወቅ እንዲሁም እንደሚጠራ ለአማኝም ይህንኑ ውጤት ማስገኘቱ ነው።
6. በመከራ ውስጥ ሳለን ሰው የዚህ ዓይነቱን አባባል ቢለን ውስጣችን ለማስገባት ሰዎች ስለሆንን እንቸገራለን፤ ስለዚህም ዘሬውኑ መንፈስ ቅዱስ ሲያስተምረን ልባችንን ከፍተን ብንማረውና አመለካከታችንን ብንቀይር ለነገ ይረዳናል።
7. ‹‹በአለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዟችሁ እኔ አለምን አሸንፌዋለሁ።›› ዮሐ 16፡33 ይህ ክፍል ከብዙዎቹ አንዱ ነው።
8. ነፍሰ ገዳይ፣ ሌባ፣ ወንጀለኛ፣ ወይም በሰው ነገር ጣልቃ የምንገባ ሆነን መከራን እንዳንቀበል ይመክረናል። ጴጥሮስ ይህንን በቃል የሚሰብከው ብቻ ሳይሆን በህይወቱ የተለማመደው ነገር መሆኑን ከሐዋ ሥራ 5፡40-41 ላይ መረዳት እንችላለን።
9. ይህ አነጋገር የሚያሳየን መከራው ለሞትም የሚያበቃ ሊሆን እንደሚችልና ክብደቱን ያሳየናል።
10. እያንዳንዱ ሃሳቡን ይናገር።

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት አስር (1ኛ ጴጥ 5፡1-14)

1. ሽማግሌ ፣ የክርስቶስ መከራ ምስክርና ወደፊት የሚገለጠው ክብር ተካፋይ መሆኑን እናያለን። የመጀመሪያ ምክሩ ሽማግሌዎቹ መንጋውን እንዲጠብቁ ነው።
2. በዮሐ ወንጌል ውስጥ ለጴጥሮስ እንደተነገረው መንጋው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ስለሚገኝ ለእያንዳንዱ ለእድገቱና ለጤንነቱ የሚያስፈልገውን ጥንቃቄ ውሰዱ የሚለውን ሃሳብ ይጠቀልላል።
3. መንጋውን ሲጠብቁ እግዚአብሄር ምን ይጠበቅብኛል የሚለውን በቅድሚያ ሊያውቁ ያስፈልጋል፤ ይኸውም በግድ ሳይሆን በፈቃደኛነት፣ ለጥቅም ሳይሆን ከልብ ካላቸው ፍላጎትና በላያቸው በመሰልጠን ሳይሆን ለመንጋው ምሳሌ በመሆን ሊሆን ይገባል።
4. ይህ መንጋ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው የሽማግሌዎቹ ወይም የማንም ሳይሆን የእግዚአብሄር ስለሆነ ነው። ፓስተርና ሽማግሌዎች ሁለቱም አንድ አይነት ሃላፊነት ያላቸው አገልጋዮች ናቸው።
5. ሽማግሌዎች ይህንን ከባድ ሃላፊነት እንዲወጡ ትልቅ ማበረታቻ ሆኖ የማየው በቁ 4 ላይ ጌታቸው ሲገለጥ የሚቀበሉት አክሊል ነው። በዚህ ቁ4 ላይ እንደምናነበው ሽማግሌዎች የመጀመሪያ ተጠሪነታቸው ለእረኞች አለቃ ለኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
6. ዕብ 13፡17 መንጋው ለመሪዎቹ በፈቃደኛነት እንዲገዙላቸው ያዛቸዋል። መንጋው ይህንን ማድረጉ ሽማግሌዎቹ በሚፈጠርባቸው ችግር ላይ ማተኮር ትተው ለነፍሳቸው የሚሆን ነገር ላይ ማተኮር ይችላሉ፤ እንዲሁም ሥራቸውን በደስታ ለመስራት ይረዳቸዋል።
7. እነዚህ ምክሮች፡- ለሽማግሌዎች እንዲገዙ፣ ትህትናን እንዲለብሱ፣ ራሳቸውን ዝቅ እንዲያደርጉ፣ ራሳቸውን እንዲገዙ፣ እንዲነቁ፣ ዲያቢሎስን በእምነት እንዲቃወሙት።
8. ሽማግሌዎቹ መንጋውን እንደገዛ ንብረታቸው አድርገው ሳያዩት በትህትናና ምሳሌነትን በማጉላት ቢያደርጉት መንጋው በቀላሉ እንዲገዛ እንቅፋቱን ያስወግዱለታል፤ መንጋው ደግሞ ስህተቱ በተነገረው ቁጥር ለምን ተነካሁ ሳይል በትህትናና መሪዎቹን በማክበር ቢመላለስ በሁለቱ መሃል ጤናማ ግንኙነት እንደሚዳብር እርግጠኛ ነኝ።
9. ለተሳታፊዎቹ ዕድል በመስጠት ሃሳባቸውን እንዲገልጡ ይሁን።